DC VOICE

# ዲሲ ቮይስ
## የተዘጋጁ ትምህርት ቤቶች ፕሮጀክት

### *ለ2007-2008 የትምህርት ዓመት የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ዝግጁነት ልዩ ሪፖርት*

በቅርቡ የመጡ የውጭ አገር ዜጎችን፣ በተለይ በብዛት ከሴንትራል አሜሪካ የመጡትን፣ አገልግሎት ለመስጠት ያለውን ችግር በተመለከተ በ1989 ዓ.ም. የዋና ሃላፊው ቢሮ የሁለት ቋንቋ ትምህርት አጥኚ ቡድን የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች የአናሳ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች አጠቃላይ እቅድ አቀረበ። ከ1989 ጀምሮ መሻሻል ቢደረግም ከዚህ የበለጠ መሆንና መደረግም አለበት። እስካሁን ድረስ የተደረገውን መሻሻል ለመገምገም የዲሲ ቮይስ በመስከረም ወር በ2007-2008 የትምህርት ዓመት የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪዎችን ለማገልገል ዝግጁ መሆናቸውን ለመገምገም የትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎችን በማነጋገር ጥናት አካሄደ።

በርካታ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ባሉባቸው ትምህርት ቤቶች - በ15 አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ አንድ ከኪንደርጋርደን እስከ ስምንተኛ ክፍል እና አንድ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ቃለ መጠይቅ አካሄደ። የትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎች ስለ ሠራተኛ፣ ስለ ትርጉምና ማስተርጎም፣ ስለ መጻህፍትና ሌሎችም የማስተማር ዘዴዎች ጥያቄ አቀረባለቸው።

- 82% ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎቻቸው አስተማሪዎችና ሌሎችም ሠራተኞች በትምህርት ዓመቱ መጀመሪያ መቀጠራቸውን ሪፖርት አደረጉ።
- 100% በዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች በአምስቱ ዋና ቋንቋዎች የተተረጎሙ የመመዝገቢያ ሰነዶችን መቀበላቸውን ሪፖርት አደረጉ።
- 77% የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎቻቸውን ለማገልገል በቂ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች እንዳሏቸው ሪፖርት አደረጉ።

| የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች | የተማሪዎች ቁጥር | % የተማሪዎች |
|---|---|---|
| የተለያየ ቋንቋና ባህል ያላቸው ተማሪዎች | 7,071 | 13.36% |
| *የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች* | 4,139 | 7.8% |
| በዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ያሉ ቋንቋዎች | 102 | |
| Data from DCPS Office of Bilingual Education, October 2007 | | |

ከዚህ በታች የሚከተሉት አስተያየቶች ከጥናቱ በተገኘው ውጤት ላይ የተመሠረቱ ናቸው።

- በትምህርት ዓመቱ መጀመሪያ መቶ በመቶ አስፈላጊው ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች አስተማሪዎች በሁሉም ትምህርት ቤቶች መቀጠራቸውን ማረጋገጥ፣
- ለትምህርት ዲሬክተሮችና በጠቅላላ ለአስተማሪዎች ስለ እንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ሥልጠና መስጠት፣
- የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች አስፈላጊው የመማሪያ ቁሳቁሶች እንዲኖራቸውና የትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎች ቁሳቁሶቹን ለመግዛት በቂ ገንዘብና ሥልጣን እንዲኖራቸው ማረጋገጥ፣
- የቋንቋ የቴሌፎን ማስተርጎሚያ መስመር አገልግሎት በየትምህርት ቤቱ በጥቅም ላይ መዋሉንና የተተረጎመው መረጃ ትክክልና ለተጠቃሚው በቀላል የሚገባ መሆኑን ማረጋገጥ፣
- የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ቤተሰቦች ልጆቻቸውን በተመለከተ የሚደረጉ ለውጦችን በተለይም የትምህርት ቤቶች መዋሀድና መጠናከርን የመሳሰሉትን የሚያውቁበት የተለየ የማስታወቂያ እቅድ ማውጣት።

የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ሪፖርት የተዘጋጀው በጋራ ከዲሲ በቋንቋና በባህል ለተለያዩ ተማሪዎች ቤተሰቦች አማካሪ ካውንስል ጋር ነው። ተጨማሪ ተባባሪዎች የሚከተሉት ናቸው። ኤስያን አሜሪካን ሊድ፣ ሴንትሮኒያ፣ ዲሲ ላንጉዌጅ አክሰስ፣ ኢትዮጵያን ኮሚኒቲ ሴንተር፣ ሚድ አትላንቲክ ኤኩቲ ኮንሶርቲየም፣ መልቲ ካልቸራል ኮሚኒቲ ሰርቪስ ሴንተርና ቬትናሚስ አሜሪካን ኮሚኒቲ ሴንተር ናቸው። ሙሉ ሪፖርቱን ለማግኘት እባክዎን በስልክ ቁጥር 202-986-8535 ወይም በድህረ ገጽ www.dcvoice.org ይመልከቱ።

የዲሲ ቮይስ ለልጆች ትምህርትና መማርን በተለይም በ2008 የተዘጋጁ ትምህርት ቤቶች ፕሮጀክቶችን በተመለከተ ከተባባሪ ድርጅቶች ጋር መሥራቱን ይቀጥላል። ለበለጠ መረጃ ወይም የነጻ አገልግሎት በRSP@dcvoice.org ወይም በስልክ ቁጥር 202-986-8535. ይጠይቁን።

---

ጠቅላላ የተዘጋጁ ትምህርት ቤቶች ፕሮጀክት ሪፖርት በድህር ገጽ www.dcvoice.org ይመልከቱ